የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፯
አዲስ አበባ — ኅዳር ፳፮ ቀን ፲፱፻፹፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 7
ADDIS ABABA – 5th December, 1996


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፶/፲፱፻፹፱ ዓ.ም.

ወደግል ይዞታ የተዛወሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) አዋጅ ........ ገጽ ፪፻፹፬


## CONTENTS


Proclamation No. 50/1996

Establishment of the Board of Trustee for Privatized Public Enterprises (Amendment) Proclamation ........ Page 284


### አዋጅ ቁጥር ፶/፲፱፻፹፱

### ወደግል ይዞታ የተዛወሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድን ማቋቋሚያ አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

ወደ ግል ይዞታ የተዛወሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድን ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ወደግል ይዞታ የተዛወሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፶/፲፱፻፹፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ማሻሻያ

ወደግል ይዞታ የተዛወሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፯/፲፱፻፹፰ እንደሚከተለው ተሻሽሏል ፤

፩· ከአንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፬) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተጨምሯል፤

"፭· የቦርዱን መዋቅርና የቦርዱ ሠራተኞች የሚተዳደሩበትን የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግን መሠረታዊ ዓላማዎች በመከተል የተዘጋጀ መመሪያ ያጸድቃል፤"

### PROCLAMATION No. 50/1996

### A PROCLAMATION TO AMEND THE ESTABLISHMENT OF THE BOARD OF TRUSTEE FOR PRIVATIZED PUBLIC ENTERPRISES PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to amend the Establishment of the Board of Trustee for Privatized Public Enterprises Proclamation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This proclamation may be cited as the "Establishment of the Board of Trustee for Privatized Public Enterprises (Amendment) Proclamation No. 50/1996."

2. *Amendment*

The Establishment of the Board of Trustee for Privatized Public Enterprises Proclamation No. 17/1996 is amended as follows:

1) The following new sub-Article (5) is added after sub-Article (4) of Article 9:

"5) to approve the organizational structure of the Board and directives on its staff regulation prepared in line with the basic principles of federal civil service laws;"

፪. የአንቀጽ ፱ የቀድሞዎቹ ንዑስ አንቀጽ (፭) እና (፮) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ (፮) እና (፯) ሆነዋል።

፫. በአንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሐ) ውስጥ "በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት" የሚለው ሐረግ ተሠርዞ "የሥራ አመራር ቦርዱ ባጸደቀው መመሪያ መሠረት" በሚለው ተተክቷል።

፫. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከኅዳር ፳፮ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ኅዳር ፳፮ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2) The former sub-Articles (5) and (6) of Article 9 are renumbered as sub-Articles (6) and (7), respectively.

3) The phrase "in accordance with the federal civil service laws" appearing in sub-Article (2) (c) of Article 12 is deleted and replaced by the phrase "in accordance with directives approved by the Board of Management"

3. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 5th day of December, 1996.

Done at Addis Ababa, this 5th day of December, 1996.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE